# የተንዳሆ ቤቶች ልማት ኘሮጀክት

ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ አገራችን ካለችበት ኋላቀር የኢኮኖሚ ዕድገት በማላቀቅ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ከሚያስችሏት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ግንባር ቀደሙ በመሆኑ የግብርናን ምርት ውጤት እንደ ዋነኛ ግብዓት ተጠቅመው በተለይም የውጪ ምንዛሪ የሚያስገኙ ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችን ማስፋፋትና ማቋቋም የመንግት ልዩ የትኩረት አቅጣጫ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡

በዚህም መሠረት በ50 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሸንኮራ አገዳን በማልማት በቀን 26 ሺህ ቶን የሸንኮራ ምርት ፈጭቶ በዓመት ከ600 ሺህ ቶን በላይ ስኳር የማምረት አቅም ያለው ግዙፉ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ኘሮጀክትን እውን ለማድረግ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከሥራው ጋር ቅርበት ያላቸውን መንግሥታዊ ድርጅቶች በማስተባበር ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የተንዳሆ ቤቶች ልማት ኘሮጀክትም ለዚሁ ኘሮጀክት አጋዥ አካል ሆኖ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

## I. የተንዳሆ ቤቶች ልማት ኘሮጀክት ጽ/ቤት አመሠራረት

በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የተንዳሆ ቤቶች ልማት ኘሮጀክት በመንግሥት የልማት ዕቅድ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጥቅምት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ መሠረት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር መጋቢት 1 ቀን 1999 ዓ.ም. ተቋቋመ፡፡

ኘሮጀክቱ በዋናነት ከመንግሥት የልማት ስትራቴጂ ማስፈፀሚያ ኘሮጀክቶች አንዱ ለሆነውና የመስኖ ግድብ ሥራው በፍጥነት እየተከናወነ ለነበረው ግዙፉ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ሠራተኞች መገልገያ የሚሆኑ 17,233 መኖሪያ ቤቶችና 308 ማኅበራዊ አገልግሎት ማስጫ ተቋማት በወጪ ቆጣቢ ዲዛይን በፍጥነት ገንብቶ እንዲያስረክብ የተቋቋመ ሲሆን፣ ከዚሁ ጋር በተያያዥነት አሣታፊ የሆነ አሠራርን በመከተል ፋብሪካው ለሚቋቋምበት ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኅብረተሰብ ሰፊ የሥራ ዕድልን የመፍጠርና ድህነትን የመቀነስ፣ ክልላዊና ሀገራዊ የኮንስትራክሽን አቅምን የመገንባት፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን የማጠናከርና የመሳሰሉ ተግባራትን የማከናወን ታላቅ ሀገራዊ ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል፡፡

የተንዳሆ ቤቶች ልማት ኘሮጀክት እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት የሚያስችሉ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን አድርጐ ከአራዳና ከየካ ክፍለ ከተማ ቤቶች ልማት ኘሮጀክት ጽ/ቤቶች የተዛወሩ 167 ሠራተኞችንና ሌሎች 138 አዲስ ሠራተኞችን በመቅጠር በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ልዩ እገዛና ክትትል በአንድ ማዕከላዊ አመራርና ኤርታሌና አዋሽ በተባሉ ሁለት ቅርንጫፎች በጽ/ቤት ደረጃ ተደራጅቷል፡፡ አዲስ አበባ ከነበሩ 36 አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት እና ከ34 የሥራ ተቋራጮች ጋር የሥራ ውል በመፈፀምም በተቋቋመ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በሚያዝያ ወር 1999 ዓ.ም. የግንባታ ሥራውን ለመጀመር በቅቷል፡፡

በተሰጠው ተልዕኮ መሠረትም በመጀመሪያው ምዕራፍ በአምስት መንደሮች 3,387 መኖሪያ ቤቶችና 61 ማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ግንባታ አጠናቆ የካቲት 2 ቀን 2002 ዓ.ም. ለምረቃ ያበቃ ሲሆን፣ ከዚሁ ጎን ለጎን የሁለተኛውን ምዕራፍ ግንባታ ሥራ

በመጀመር በሰባት መንደሮች የ5,610 የመኖሪያ ቤቶችና የ85 ማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታ በመፋጠን ላይ ይገኛል፡፡ የተንዳሆ ቤቶች ልማት ኘሮጀክት እስካሁን ባከናወናቸው ተግባራት በርካታ ሀገራዊና ክልላዊ ጠቃሜታዎችን አስመዝግቧል፡፡

### ሀ/ ሀገራዊ ጠቀሜታዎች

የተንዳሆ ቤቶች ልማት ኘሮጀክት ከሌሎች ሀገር አቀፍ የተቀናጀ የቤቶች ልማት ኘሮግራሞች ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ወጪ ቆጣቢ በሆነ ቴክኖሎጂና ውጤታማ በሆኑ አማራጭ የግንባታ ማቴሪያሎች በመጠቀም ሀገራዊው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲያድግ ያደረገውና ወደፊትም የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ላቅ ያለ ነው፡፡ በሌላም በኩል በርካታ ቁጥር ያላቸው ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በኘሮጀክቱ ውስጥ በሰፊው እንዲሳተፉ በማድረግ አቅማቸው እንዲጎለብትና የገበያ ዕድል እንዲፈጠርላቸውም በማድረግ፣ መንግሥት በመላ ሀገሪቱ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ለማስፋፋትና ሥራ አጥነትን ለመቀነስ ለሚያደርገው ጥረት ትልቅ ድጋፍ አበርክቷል፡፡

በልማት ኋላቀር በሆነው የአርብቶ አደሩ አካባቢ ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በመደረግ ላይ ለሚገኙት የልማት ጥረቶች የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ረገድም፣ ኘሮጀክቱ ቤቶችንና ማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በሚገነባባቸው አካባቢዎች እንደ ንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ መንገድ፣ ትምህርት ቤት፣ ጤና ጣቢያ፣ ጤና ኬላ፣ ኤሌክትሪክ፣ ስልክና የመሳሰሉ የመሠረተ ልማት አውታሮች በሚመለከታቸው አካላት እንዲስፋፉ በማድረግ በተለይም የአርብቶ አደሩን አካባቢ የመሠረተ ልማት ሽፋን በማሳደግ ታላቅ ጠቀሜታን አስገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የተንዳሆ የቤቶች ልማት ኘሮጀክት መንግሥት ከተሞች ውሃ ባለበት አካባቢ እንዲቆረቆሩ የቀየሰውን ዕቅድ እውን ከማድረጉም ባሻገር፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ለማስፋፋት እየተደረገ ላለው ጥረት ትልቅ ድጋፍ አበርክቷል፡፡

የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ወደ ምረት ተግባር እንዲገባ ምቹ የሥራና የመኖሪያ አካባቢን በመፍጠርም ኘሮጀክቱ ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ ድጋፍ ከማበርከቱም በተጨማሪ፣ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የአብሮ የመኖር ባህልን እንዲያዳብሩ፣ የባህልና የሥራ ልምድ እንዲለዋወጡና አካባቢው የልማት ማዕከል እንዲሆን አስችሏል፡፡

### ለ/ ክልላዊ ጠቀሜታዎች

የተንዳሆ ቤቶች ልማት ኘሮጀክት ተልዕኮ ሲቀረጽ እንደ ወሳኝ ነጥብ ተደርጎ የተወሰደው የክልሉን ሕዝብ በኘሮጀክቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግም የኘሮጀክት ጽ/ቤቱ በቅድሚያ የክልሉን ኅብረተሰብ አሳታፊ የሚያደርግ አሠራር ለመዘርጋት የሚያስችል ዕቅድ በመንደፍ የጀመረ ሲሆን፣ እስካሁን ባለው የሥራ ሒደትም ለአፋር ብሔራዊ ክልል ኅብረተሰብ የሚከተሉት ዓበይት አስተዋጽኦዎች አበርክቷል፡፡

- የክልሉ ተወላጆችና ነዋሪዎች ከአነስተኛ የሥራ መደቦች ቅጥር ሥራ እስከ ሥራ ተቋራጭነት ባለው የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ከመሆናቸው ባሻገር ቀደም ሲል ያልነበረ የሥራ ባህል እንዲፈጠርና እንዲዳብር አስችሏል፡፡

- በመጀመሪያው ምዕራፍ የግንባታ ሒደት 465 የክልሉ ተወላጆች (ከጠቅላላ የኘሮጀክቱ ሠራተኞች 72.43%) በኘሮጀክቱ ውስጥ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በቀጣይ

የግንባታ ምዕራፎችም ይህንን የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት የማረጋገጡ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

- ቁጥራቸው አነስተኛ የማይባል የክልሉ ነዋሪዎች የግንባታ ማሽነሪዎችን እና ተሽከርካሪዎችን ከማከራየት ጀምሮ በተለያዩ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች እንዲሰማሩ ከማስቻሉም በተጨማሪ፣ የክልሉ ባለሀብቶች ንብረት የሆኑ ከ80 በላይ ተሽከርካሪዎችን በኪራይ በፕሮጀክቱ ላይ በማሳተፍ ሀብታቸውን እንዲያዳብሩና ጥሪት እንዲፈጥሩም አመቻችቷል፡፡

- የክህሎት ሽግግርን በተመለከተ በርካታ የክልሉ ተወላጆችን በፕሮጀክቱ ሥራ ተሳታፊ በማድረግ የልዩ ልዩ ክህሎቶች ባለቤት እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

- የክልሉን የኮንስትራክሽን አቅም በመገንባቱ ረገድ፣ በመጀመያው ምዕራፍ ከ70 ያላነሱ የሥራ ተቋራጮች በፕሮጀክቱ ሥራ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ ይህ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር ተደርጓል፡፡ ከክልሉ አስተዳደርና ከናማሌፋን ተንዳሆ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጋር በመቀናጀት በተለያዩ የኮንስትራክሽን ዘርፎች ከሦስት ሺህ በላይ ሠልጣኞችን በግንበኝነት፣ በአናፂነት፣ በኤሌክትሪክ፣ በቀለም ቅብ፣ በብየዳ፣ በልሰና፣ በብሎኬት ሥራ፣ በአግሮስቶን ገጠማና በሳኒተሪ ሥራዎች ሠልጥነው በፕሮጀክቱና በክልሉ በሚካሔዱ የግንባታ ሥራዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ተድርጓል፡፡ ይህም በአንድ በኩል የሥራ አጥነትን ችግር በተወሰነ ደረጃ ሲያቃልል በሌላ በኩል በግንባታ ሥራዎች ላይ የሚታየውን የባለሙያ እጥረት ክፍተትን ለመድፈን አስችሏል፡፡

- ከፕሮጀክቱ ተቀዳሚ ዓላማዎች አንዱ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በተቋቋሙበት የሙያ ዘርፍ አዳዲስ የሥራ መስኮችን ፈጥረው ራሳቸውን ወደ ሥራ ፈጣሪነት /ኢንተርፕርነርነት/ በማሳደግ የሀገርና የወገን ልማት እንዲፋጠን ማድረግ በመሆኑ፣ የአካባቢውን ሥራአጥ ኅብረተሰብ በተለያዩ ሙያዎች በማደራጀትና የገንዘብና የሙያ ድጋፍ በመስጠት አቅም የማጐልበትና የሥራ ዕድል የመፍጠር ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም መሠረት 193 ማኅበራት በመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ በብሎኬት፣ በኘሪካስት፣ በኤሌክትሪክ፣ በሳኒተሪ፣ በብረታ ብረት፣ በመስታወት ገጠማ እና በመሳሰሉት ሥራዎች ላይ የተሳተፉ ሲሆን ሌሎች ተጨማሪ 85 ማኅበራትም በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ተደራጅተው በሁለተኛው ምዕራፍ የግንባታ ሥራ ላይ ለመሳተፍ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሥራ ላይ ከተሠማሩት 193 ማኅበራት መካከል 130 ማኅበራት (67.4 %) በክልሉ ተደራጅተው ወደ ሥራ የገቡ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ኘሮጀክቱ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አማካኝነት ከ3,500 በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የሥራ ዕድል የፈጠረ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል 2,510 ሰዎች በማኅበራት በመደራጀትና 1,056 ሰዎች ደግሞ በማኅበራቱ በመቀጠር የሥራ ዕድል ያገኙ ናቸው፡፡

- ቀደም ሲል በጥቅም ላይ ያልዋሉ እንደ ቀይ አሸዋ፣ ነጭ አሸዋ፣ የድንጋይ ኳሪዎችና እነዚህን የመሳሰሉ ማዕድናት ሥራ ላይ ውለው ለኅብረተሰቡ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

- የመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ በተካሔደባቸው አምስት መንደሮች እንደ መንገድ፣ ውሃና የመሳሰሉት የመሠረተ ልማት አውታሮች ከመዘርጋታቸውም በተጨማሪ ማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትም በመጠናቀቃቸው አገልግሎት በሚጀምሩበት

ወቅት የአርብቶ አደሩ ኅብረተሰብና ልጆቹ አስተማማኝ በተጓዳኝ የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች አገልግሎቶች ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

## II. የመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ ውጤቶች

ከቅድመ ዝግጅት ጀምሮ የግንባታ ሥራዎቹን በተለያዩ ሒደቶች ሲያከናውን የቆየው የተንዳሆ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በመጀመሪያው ምዕራፍ በአምስት መንደሮች የ3,387 መኖሪያ ቤቶችንና የ61 ማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታ አጠናቋል፡፡ ከእነዚህም መካከል 2 ጤና ጣቢያዎች፣ 3 ጤና ኬላዎች 5 አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ 2 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ 2 አዳራሾች፣ 2 ፖሊስ ጣቢያዎችና 5 መጋዘኖች ይገኙበታል፡፡

የተንዳሆ ስኳር ፕሮጀክት ከሚፈልገው ግዙፍ ካፒታል አንፃር የግንባታ ወጪውን መቀነስ ፕሮጀክቱ ውጤታማ እንዲሆን ከመርዳቱም በላይ ለሀገር ኢኮኖሚ ያለውን ጠቀሜታ በመረዳት የተንዳሆ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት የሚገነባቸው ሕንፃዎች ዲዛይኖች ወጪና መሬት ቆጣቢ ተደርገው የተዘጋጁ ሲሆን፣ ሕንፃዎች የአካባቢውን የአየር ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት እንዲገነቡም ተደርጓል፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ ተገንብተው ለምረቃ የበቁትና በቀጣይም የሚገነቡት ሕንፃዎች የከተሞች ቤት አሠራርን (Town House) እና የቪላ ሕንፃ ዓይነቶችን አካተው የያዙ ሲሆኑ፣ ከፍታቸውም የመኖሪያ ሕንፃዎቹ ከ G+0 እስከ G+2፣ የማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማቱ ደግሞ ከG+0 እስከ G+3 ይደርሳል፡፡

***/የመጀመሪያውን ምዕራፍ ግንባታ የምርቃት በዓልና ግንባታዎቹን About Us በሚለው ርዕስ ሥር Photo Gallery ላይ ይመልከቱ/***

## III. ቀጣይ ተግባራት

የተንዳሆ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ለምረቃ ካበቃቸው የመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታዎች በተጓዳኝ ከመስከረም 1 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ በምዕራፍ ሁለት ለመገንባት ያቀዳቸውን 5,610 ቤቶችን እና 85 ማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ከተሟላ የመሠረተ ልማት አውታር ጋር በአንድ ትልቅ ከተማ፣ በአንድ መካከለኛና በአምስት መንደሮች በ132 የሥራ ተቋራጮችና በ10 አማካሪዎች በ10 ወራት ጊዜ ውስጥ ገንብቶ ለማጠናቀቅ አስፈላጊውን ሁሉ ቅድመ ዝግጅት አድርጐ ወደ ሥራው የገባ ሲሆን፣ ግንባታውም በመፋጠን ላይ ይገኛል፡፡

ይህ ምዕራፍ በመጀመሪያው ምዕራፍ የግንባታ ሒደት የታዩ ጠንካራና ደካማ ጐኖች ተገምግመው መልካም ተሞክሮዎች የተቀመሩበት፣ እንዲሁም በርካታ የተሻለ አቅም ያላቸው ሥራ ተቋራጮች፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እና አማካሪዎች የተሳተፉበት በመሆኑም ግንባታዎቹ ጥራታቸውን ጠብቀው በ2002 መጨረሻ ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

# A Huge Project Deemed to Stimulate Socio-economic Transformation

**The Ethiopian Herald**
**Thursday Feb. 18, 2010**

The Ethiopian government has designed and adopted agriculture led industrial development strategy (ADLI) so as to accelerate sustainable economic development and get rid of backward economic growth to join middle income countries in the next 20 years. One of the objectives of the policy is the achievement of industrial competitiveness in areas of clear comparative advantage in industrial exports. Accordingly, the government has given due emphasis to the expansion and establishment of export-oriented factories that use agricultural products as raw material and generate foreign currency. The establishment of Tendaho sugar factory which utilizes sugar cane as the main raw material is also the result of this policy. Upon completion, the factory will have a capacity to produce more than 600,000 tons of sugar annually making it the largest African in terms of capacity. The main objective of this project is to increase the national sugar production both for local and export market and improve the livelihood of the communities; which will be affected or residing nearby the project area throughout grower and other interrelated interventions.

The establishment of the sugar factory has included three supplementary projects-Kesem Tendaho irrigation project, Tendaho housing development project, and Tendaho sugar cane plantation. The Kessem-Tendaho project comprises two irrigation development sites at Kessen and Tendaho with an area of 65,000 hectare and 25,000 hectare respectively; which totals 90,000 hectare. The project started on July 2004 and it is located in the Awash Basin. The project included Tendaho Dam project, the largest dam constructed by the Water Works Construction Enterprise which has a capacity to hold 1.8 billion cubic meters of water. The project has also sugar cane plantation project on more than 60 thousand hectare of land. The construction of the dam and the preparation of the land for the sugar plantation, both undertaken by the Ministry of Water Resources, were also well underway according to plan.

The Tendaho housing development project was launched by the request of the federal government as one of the supplementary projects to speed up execution of Tendaho sugar factory project in 1999. The housing project was planning to construct 17,233 houses and 308 common facilities for Tendaho sugar factory employees and management. The houses were to be built in the Afar State in a 70 km range from Dubti to Assaita.

Recently, the housing project office inaugurated the first phase 3,387 housing units and 61 common facilities in five areas/blocks located between Dubti and Assaita towns of the Afar State. Trade and Industry Minister Girma Birru said the level of progress so far in the housing development project is well in progress along with the sugar manufacturing plant establishment and sugar cane plantation. As the area is very close to the port, it would help promote sugar export and cover local consumption as well.

In addition to its supplementary contribution to the sugar factory establishment, the housing project has brought about extensive benefits both at regional and national level. Girma said the federal government established the sugar factory in Afar State with two basic objectives in mind. The first is to cover the local sugar consumption and the sugar export need of the country. Upon completion, the sugar factory by itself will produce twice the current sugar production of the country. The second is to improve the economic condition of the Afar State from its base. The project will also significantly help Afar have a modern city. Besides improving the country’s sugar supply, the establishment of the factory would turn the area into a better economic centre, he emphasized.

The Minister noted that the establishment of the overall project in the region would benefit the local community in so many ways. They would be benefited in getting employment opportunities and it would serve as a market centre for the local consumers as the project improves infrastructure in the area. A town with a population of 150,000 to 200,000 is expected to evolve. Hence, the local pastoral community who are living around the sugar plantation area would be able to get a market for their products especially for their cattle and cattle products. This would enable them to be sedentary farmers.

The housing project is mainly undertaken under the supervision of the Ministry of Works and Urban Development. State Minister of Works and Urban Development Arkebe Equbaye said that the sugar factory is one of the biggest in Africa and the Ministry had been involved in the project in the construction of residential houses, social infrastructures, police stations, clinics and the likes for employees of the factory.

He said the second phase of construction is also under progress and based on the experiences gained from phase one, the construction time and quality standard will be improved. Because phase one was done under difficult condition where so many infrastructural facilities were not met.

In terms of housing design, he said, many local factors have been taken into consideration. In addition, other factors like the weather and cost have been given top priority. “In the process, he said, we faced many problems including shortage of skilled manpower and logistical constraints. The weather was a little bit harsh. But generally speaking, these were not huge problems that could not be solved,” he added.

According to the General Manager of the project, Mitiku Habena, the country’s agriculture-led development policy focuses on the establishment of factories that generate foreign currency, and the Tendaho project is included in this category, adding that, in addition to the sugar factory, the construction of the housing units has also a vision to develop the country’s construction industry.

Since the Afar State is among the most backward states in the country, the establishment of the project created a huge economic initiative in the region.

The project contributed a lot in changing the lives of the local community by improving the economic activity in the area. The local community, mainly the youth has benefited from the project by directly participating in the construction of houses as contractors and producing and supplying raw materials for the project by organizing themselves in small and micro-finance unions. Moreover local investors have also participated by renting various materials, machinery and vehicles for the project. The project has rented more than 80 automobiles from local investors. These activities have improved the saving and investment culture of the community.

The housing project has also brought about infrastructural developments like hospitals, road, electricity, telecommunication and pure drinking water provision to the area. In the first phase of the project 5 health stations, 5 elementary and 2 secondary schools, 2 city halls and police stations and the likes were built. Moreover in the first phase more than 465 members of the local community which account for 72.43% of the total project employees have got employment opportunity. The project has also created skill development training opportunities for 3,000 local community members.

Generally, 55 local contractors participated in the construction of the housing units and common facilities. Some 193 unions many of which were from Afar State also participated in the project by engaging in the production of bricks, precast, electricity installments, sanitary, metal and other works. Generally, the project has created more than 3,500 employment opportunities through small and micro-finance enterprises.

In the second phase the project is planning to construct 56190 houses and 85 common facilities in additional seven blocks/areas. Especially, block 18 of the second phase project which is going to be built in Assaita, will include more than 3,000 houses, one standardized hospital and 23 common facilities and is believed to speed up the growth of the town.

***/See the photographs of the 1$^{st}$ phase inauguration ceremony, the construction site, and the buildings on the Photo Gallery page under About Us/***